# ኢ.ሕ.አ.ፓን አንድ የሚያደርግ ወይስ ስም ቀያሪ ጉባኤ?

ነሲቡ ስብሐት (አሉላ) ሐምሌ 21 ቀን 2007 ዓ.ም.

ውድ ወገኖች! ሰኔ 25 ቀን 2007 ዓ.ም. የወጣውን የኢ.ሕ.አ.ፓ ዴ ጋዜጣዊ መግለጫ እዚህ ተጭነው ያንብቡ።

http://eprp-ihapa.com/images/Pressreleases/EPRP-ANDNET.Press.release.pdf

"ኢ.ሕ.አ.ፓን አንድ ለማድረግ የተደረገው ልዩ ጉባኤ በድል ተጠናቀቀ" ተብሎ የተለቀቀውን ጋዜጣዊ መግለጫ ሳነብ መንፈሴ "ጠቀሜታው ለምን?" ብሎ ቢረበሽም ስለ ኢ.ሕ.አ.ፓ የሚንገበገቡና ሁሉም የኀብረተሰብ ክፍል ስለ ጉዳዩ በግልጽ ማወቅ አለባቸው ከሚል ሀሳቤን ላስነብብ ፈለግሁ።

የኢትዮጵያ ሕዝባዊ አብዮታዊ ፓርቲ (ኢ.ሕ.አ.ፓ) በአወንታዊም ሆነ በአሉታዊ ጐኑ ስሙ ሲነሳ በርካታዎችን ይነካል። ከዛሬ 40 ዓመታት በፊት ነሐሴ 26 ቀን 1967 ዓ.ም. እራሱን ለኢትዮጵያ ሕዝብ ይፋ ያደረገው ኢ.ሕ.አ.ፓ ታሪኩ የሀገርና የሕዝብ ነውና ስለ ኢ.ሕ.አ.ፓ በሚወጡ ጽሑፎች፣ መጽሐፎች ላይ አስተያየትን በመስጠት የድርጅቱን ታሪክ መከላከል የሚያስፈልገው ሕዝባዊነቱንና ኢትዮጵያዊነቱን ከቶም ለጥያቄ ያቀረበ ፓርቲ ባለመሆኑ ነው። ኢ.ሕ.አ.ፓ ሲነካ ያለአግባብ ሲተች ቆመው የሚሄዱ፣ በውስጡ ያለፉ ብቻ ሳይሆኑ የሰማዕታት ሙታን ዓጽም ይላወሳል። የሙታን ድምጽ ከመቃብር ይጮሃል።

ኢ.ሕ.አ.ፓን ጥላሸት እየቀቡ ያሉ የፋሽስት ደርግ ርዝራዦችን ለመከላከል ያለው አማራጭ ያደረጉትንና የሰሩትን አውሬአዊ ድርጊት ብቻ ከወረቀት ማገናኘት በቂ ነው። የግፍ ባህራቸው ተጽፎ ባያልቅም ብዕርን ከወረቀት ለማገናኘት የደፈሩ በጣም ጥቂት ናቸው። የኢ.ሕ.አ.ፓና የዚያ ትውልድ ታሪክ ተዳፍኖ እንዲቀር "እሱን አታንሱት" ባዮች ዛሬ ዛሬ ደርግና ኢ.ሠ.ፓ.ዎች ብቻ ሳይሆኑ ኢ.ሕ.አ.ፓ ነበርን ነንም ባዮች ሲሆኑ መታዘብ ከጀመርሁ ቆየት ብያለሁ። ከደርግ ጉያ ተወሽቆ የቀይ ሽብርን ቡኮ አብኩቶ መጋገሩ ላይ አብሮ ሰለባ የሆነው መኢ.ሶን ጋር ለመተቃቀፍ ሲባል የኢ.ሕ.አ.ፓ ሕዝባዊ ታሪክና የመኢ.ሶን ደርጋዊ ታሪክ ይዳፈን ዘንድ የሚመኙ አሁንም ኢ.ሕ.አ.ፓን መሪነን ባዮች ጭምር መስማትና ማየት ያሳፍራል።

ኢ.ሕ.አ.ፓ የዛሬ 40 ዓመት ይፋ ሆኖ በአጭር ጊዜ ያገኘውን ሕዝባዊ ድጋፍ መሠረት በማድረግ ለሥልጣን ያልበቃው የራሱም ደካማ ጐኖች አስተዋጽዎ ማድረጋቸው አይካድም። በዚህ ጽሁፍ በዝርዝር ማቅረብ ባይቻልም በአጠቃላይ በወቅቱ በአንድ በኩል ከፋሽስታዊው ደርግ በሌላ በኩል በተገንጣይ ጠባብ የብሔረሰብ ቡድኖች ከሚደርስበት ጥቃት በተጨማሪ ውስጣዊ ችግሩ የድል በሩ ይከረቸምበት ዘንድ አስተዋጽዎ አድርጓል። ዛሬም ላይ ሆነን ስናየው ኢ.ሕ.አ.ፓ አሁንም ከራሱ ችግር ያልተላቀቀ ከጠላት ምት እርቆ እንኳ እርስ በርሱ ያለው ሽኩቻ ቀስፎ ይዞታል።

ኢ.ሕአፓ በጥቅምት 18 ቀን 2000 ዓ.ም. (October 29, 2007) ለሁለት መከፈሉ የአባላትን ስሜት ብቻ ሳይሆን ያንኳኳው የቀድሞ አባላቱንም ጭምር ሲሆን ሰፋ አድርገን ስናየው ደግሞ በጥቅሉ የኢትዮጵያን ሕዝብ ያሳዘነና ቅስም የሰበረ ለመሆኑ አይተናል። ታዝበናል።

የድርጅቱ ነባር አመራር ላይ ያነጣጠረው የፓርቲው ውስጣዊ ችግር ምክንያት የዛሬ ሰባት ዓመት ከዘጠኝ ወር ለሁለት የተከፈለው ኢ.ሕአፓ ሌላ ስህተት አስመዝግቧል። የዚህ ለሁለት መከፈል ውጤት አባላቱንም ሆነ በቅርብ እርቀት የሚከታተሉትን ደጋፊዎቹን አሳዝኗል። "ኢ.ሕአፓ በመከፈሉ የትኛውም ወገን አሸናፊ ሊሆን እንደማይችል" የተናገሩና የተነበዩ ዛሬ ልክናቸው ቢባል ሚዛን ይደፋል። መከፈሉ የጥንካሬ ምልክት አልነበረምና።

የዚህ ጽሁፍ ዓላማ "ኢ.ሕአፓ ለምን ተከፈለ?" የሚለውን ለመተንተን ሳይሆን መከፈሉ የአደባባይ ምስጥር መሆኑን አሳውቄ ስለ አስቂኙና አስገራሚው ቅጥፈት ትዝብቴን ለማካፈል ነው። የፓርቲው መከፈል በሁለቱም ኢ.ሕአፓዎች በኩል አንደኛው አንዱን "አምባገነን" ሌላኛው "አንጃ" ይበል እንጂ እውቅና የተሰጠውና በየጊዜው ያነታረከ ጉዳይ ነው። አንዱ ኢ.ሕአፓ የሚለውን ነባር ስሙን እንደያዘ ሌላኛው ዴ ጨምሮበት ኢ.ሕአፓ ዴሞክራሲያ ብሎታል። ይኸው ነው በቃ!

ከክፍፍሉም በኋላ ዴሞክራት ነኝ ያለው ክፍል እስከነ ችግሩ በመከፈሉ አባላቱን ይዞ ለመቀጠል ውሃ መጨበጥ ሲሆንበት ዓመትም አልሞላው። መሠረታዊ የፓርቲውን ችግሮች አስውግዶ ለማጠናከር ከመቀጠል ይልቅ የችግሩ ፈጣሪዎችን አሁንም እንኮኮ ማለቱ ወደ ባዶነት ሲለውጠው ጊዜም አልፈጀበት። በክፍፍሉ የተጋሩ አባላት ለድርጅቱ ችግሮች መስተካከል እንጂ የመክፈል አባዜ ባለመሆኑ ከተከፈለው ኢ.ሕአፓ ዴ እራሳቸውን ለማግለል ተገደዋል። ኢ.ሕአፓ ዴም ስም ብቻ ይዞ መጓዝ ዕጣ ፈንታው ሆነ።

ኢ.ሕአፓን ሳውቀው ቅጥፈትና ማጭበርበር አላስተማረኝምና ያልተተገበረ ድርጊት እንደተደረገ ሲጻፍ፣ ሲወራ ህሊና ይቆጠቁጣልና፣ መቀበል ይከብዳልና ብዕሬ ወረቀት ላይ አርፏል። "ኢ.ሕአፓ አንድ ሆነ፣ እንኳን ደስ ያላችሁ" ባዮችን ሁሉንም ማስረዳት ይከብዳልና ነገሩን እስከማውቀው እንዲህ ነው። ኢ.ሕአፓ አሁንም ሁለት ነው። አንድ ሆነ የተባለው ውሸት ነው።

ከቅርብ ወራት በፊት ኢ.ሕአፓን አንድ የሚያደርግ እንቅስቃሴ እየተባለ በየድረ ገጹ የሚወጡ ጽሁፎችን ማየት ብቻ ሳይሆን ለግሌም ተነግሮኛል። መቼም ተከፍሎ የትም አልደረሰምና፣ እስቲ ልቦና ከተገኘ ተከፍሎ የተመዘገበ ጥንካሬ የለምና፣ ሀገራችን አሁን ካለችበት አጣብቂኝ ችግሮች አንፃር፣ ደካማ ጐኖችንም ይዞ አንድ ሆኖ መቀጠሉ ትንሽም ቢሆን ከሠራ እስቲ ይሞከር ብዬ ትዝብት ልወርስ ጠበቅሁ። ሂደቱን ተከታታይ ሆንሁ።

በግልጽ ለማስቀመጥ በአቶ እያሱ ዓለማየሁና በአቶ ፋሲካ በለጠ የሚመራው ኢ.ሕአፓ በአንድ በኩል፣ ዛሬ ከአመራር ለቅቄአለው ቢሉም ከበስተጀርባ በአቶ መርሻ ዮሴፍ የሚመራው ኢ.ሕአፓ ዴ በሌላ በኩል መኖሩ ለአንባቢያን ግልጽ ሊሆን ይገባል። ታዲያ ለአለፉት ሰባት ዓመታት ተከፍሎ ያለው ኢ.ሕአፓ ወደ አንድነት ጉዞ ሲጀምር ለማንም

ታዛቢና የድርጅቱ አፍቃሪ የአቶ ኢያሱ አመራርና የአቶ መርሻ አመራር ለድርድር ቀርበው በሚያደርጉት የጋራ ስምምነት ላይ የሚደረግ ግብ መሆኑን ማንም ይረዳዋል። ቢቻል ድርጅቱ ለመከፈል ያበቃውን ሁኔታዎች በደንብ ገምግሞና ለማስተካከል ዝግጅቶች ተደርገው አንድ መሆን፣ አለያም ዛሬ ሀገራችን ኢትዮጵያ እንደ ኢትዮጵያ መቀጠሏ ጉዳይ አጠራጣሪ በሆነበት ወቅት ለሀገር ሲባል በጋራ መሥራታችን ይጠቅማል፣ መከፋፈላችን ለጠላት ተመቸው እንጂ ምንም አልፈየደልንም፣ መከፋፈላችን አባላቶቻችንን እያራቀ ደጋፊዎቻችንን ከማሳዘን ሌላ ያመጣው ውጤት የለምና ችግሮቻችንን ወደ ሁለተኛ ደረጃ ዝቅ አድርገን በጋራ ለመሥራት "ይቅር እንባባል" ተብሎ የአንድነቱ ሂደት ይጀመራል።

ይህንን የኢሕአፓ አንድነት ተግባራዊ ለማድረግ በሚጀመር ከሁለቱም ኢሕአፓዎች የተውጣጣ ኮሚቴ ቅድመ ዝግጅቱን አጠናቆ ለጉባኤ ይቀመጣል። ጉባኤው በሁለቱም በኩል ያሉትን አባላትን አካቶ ከተቻለ እንደገና ሊቀላቀሉ የሚፈልጉትን ቀደምት አባላት አካቶ ሊካሄድ ይችላል። ይህን ግልጽ ለማድረግ የምፈልገው ግራ እየተጋባ ላለው የኅብረተሰብ ክፍል እንጂ ኢሕአፓን በማታለልና በማጭበርበር "አንድነት" ላሉት ለማስረዳት አይደለም። እነሱ አውቀው ተኝተዋልና። ትናንት በዴሞክራሲ ጐናቸው ዛሬ በአንድነት ስም እየተገላበጡ በሚገባ አሸልበዋል። ከህመማቸው አላገገሙም።

ውድ አንባቢያን! በአጭሩ አሁንም በአቶ ኢያሱ ዓለማየሁ የሚመራው ኢሕአፓ እራሱን ችሎ እየተንቀሳቀሰ ነው። በአቶ መርሻ ያለው ደግሞ አንድ የሆነው ከማን ጋር እንደሆነ ባይገባኝም አሁንም ኢሕአፓ ሁለት ነው። "ኢሕአፓን አንድ ለማድረግ የተደረገው ልዩ ጉባኤ በድል ተጠናቀቀ" ተብሎ ለሕዝብና ለሀገር የውሸት መግለጫ ሲወጣ እውን አያሳፍርም? እውን እኚህ ኢሕአፓ ዴዎች ችግር ላይ ናቸው? አያሰኝም። አለያም ያወጡትን መግለጫ በግልጽ ማስቀመጥ። "ከእንግዲህ አቶ እያሱ ዓለማየሁና አቶ ፋሲካ በለጠ የሚመሩትን ኢሕአፓ አንቀበልም፤ ኢሕአፓ ማለት እኛ ብቻ ነን አሁን ዕድገት በማስመዝገባችን ከ"ዴሞክራሲ" ወደ "አንድነት" ተሸጋግረናል. . ." ብሎ እቅጩን መናገር አይበጅምን? ኢሕአፓ በቅጥፈት፣ በማታለል፣ በማደናገር አንድ አይሆንም።

ውድ አንባቢያን! ያም እኔ ልክነኝ ይኸኛውም እኔ ልክነኝ ቢልም አሁንም ሁለቱ ኢሕአፓዎች ለየብቻ እየተጓዙ እንደሆነ ይታወቅ ዘንድ ድምጼን አሰምቻለሁ፣ አስነብቤአለሁ። የወጣውን መግለጫ እያነበባችሁ የአቶ እያሱና የአቶ መርሻ ኢሕአፓ ወደ አንድነት የመጣ ለመሰላችሁ ውሸት ነው። ለምን እንደፈለጉት ባይገባኝም የኢሕአፓ ዴ ያወጣው "በድል ተጠናቀቀ" የአንድነት መግለጫ ነገ የሚያፍሩበት ነው። አሁንም ሁለት ዴሞክራሲያ ዕትም መውጣቱን ትንሽ ቆይታችሁ ታያላችሁ። አሁንም በኢሕአፓ ስም በሁለቱም በኩል ጋዜጣዊ መግለጫ ሲወጣ ትመለከታላችሁ። በዚህ ጉዳይ ደግሞ አቶ እያሱ ያሉበት ኢሕአፓ ይህን ሁኔታ ለሕዝብ ግልጽ ያደርጋል ብዬ እጠብቃለሁ።

የኢሕአፓን አንድ መሆን ባልጠላም በማታለል ግን አይደለም። "ኢሕአፓን አንድ የሚያደርግ ስምፖዚየም ተካሄደ" ብሎ በማግስቱ ዋናውን የኢሕአፓ አካል ሳያካትት "ጉባኤ አካሂዶ በድል ተጠናቀቀ" ብሎ መግለጫ ማውጣት ታዛቢ ወገኖችን መናቅ ነው።

"የዳቦ ስም" እንዲሉ "ኢ.ሕአፓ ዴ"ን "ኢ.ሕአፓ አንድነት" በማለት ሳይሆን በሥራ ነው ለውጥ የሚመጣው። እንደውም የውሸት አድማሳችሁ እንደ እኔ ላለው ጥንካሬአችሁን ሳይሆን አሁንም ምን ላይ እንዳላችሁ ነጋሪና መስካሪ ነው። የጥንካሬአችሁ መለኪያ ሚዛኑ ውሸትና ቅጥፈት መሆን አይገባውም።

ሌላው ሳልገልጸው የማላልፈው ለበርካታ ዓመታት እየተከበረ ያለው የኢ.ሕአፓ ሰማዕታት ቀን "ኢ.ሕአፓ አንድነት" በተባለ ማግስት ተከፍሎ ሁለት ቦታ መካሄዱ ነው። የሰሜን አሜሪካ ኢትዮጵያውያንን እግር ኳስ ዝግጅት ምክንያት አድርጎ በየዓመቱ የሚካሄደው ይህ ዝግጅት ከፖለቲካ ወገንተኝነት ነፃ ሆኖ በትግሉ የተሰዉ ወገኖቻችን የሚታሰቡበት፣ የሚዘከሩበት በሁሉም ኢ.ሕአፓ ልጆችና ደጋፊዎች በጋራ የሚከበር መዘክር ነው። አንድ እህቴ እንባ እየተናነቃት እንዳለችኝ "ይህ ዝግጅት እኮ በየዓመቱ ለቅሶ የምደርስበት ነው። እንዴት ለቅሶ ቤት ይከፈላል?"

ይህ በየዓመቱ የሚካሄደው የቀድሞ አባላት ምሽት በ 1978 ዓ.ም. (1985/86) በዳላስ ተጀምሮ ከዓመት ዓመት ስፋትና ትኩረት እየሳበ እነሆ 29 ዓመቱን አስቆጥሯል። የኢትዮጵያውያን እግር ኳስ ዝግጅትን ተንተርሶ የሚካሄደው የቀድሞ ኢ.ሕአፓ አባላት መሰባሰቢያ ምሽት ላይ በአባልነት ያሉትን ጨምሮ የቀድሞዎቹም የቻሉ ከነቤተሰባቸው፣ ሌሎች ከነጓደኞቻቸው የሚገኙበትና ያለፈውን እያስታወሱ በተለይ በትግሉ ሜዳ ዛሬ በሕይወት የሌሉቱ ብርቅዬ ወገኖቻችንን እየዘከሩ በጋራ ጽዋ የሚያነሱበት መድረክ ነው።

ሁሉም ወገን ከአንድ መዓድ ይቆርሳል። በኢ.ሕአፓነቱ ብቻ ሁሉም በአንድ ጽዋ ይጠጣል። የተነፋፈቀው ይተቃቀፋል። ይላቀሳል። ያለፈ የትግል ትዝታን እያነሱ የሚያወጉትም ቀላል አይደሉም። ምሽቱ አዝናኝ በመሆኑም እከሌ ከገሌ ሳይባል አብሮ ይጨፍራል። በአንድ ጠረጴዛ አብሮ ይወጋል። ዝግጅቱ ሲጠናቀቅም የከርሞ ሰው ይበለን ተብሎና ተባብሎ ሁሉም በሰላምና በፍቅር ይለያያል። ይሰነባበታል። ደስ የሚል መሰባሰቢያ። እሰየው የሚያሰኝ መገናኛ። ለሌሎች አርአያ መሆን የሚገባው መድረክ።

ኢ.ሕአፓ ለሁለት ተከፍሎ በነበረው የመጀመሪያው የዚህ ዝግጅት ላይ እንኳ በጋራ ነው የተካሄደው። መከፈሉ ትኩስ በሆነበት ወቅት እንኳ በጋራ ነው የዘከርነው። ምነው ዛሬ? "አንድነት" እያልን የሰማዕታት መዘክርን ሁለት ቦታ እናከብራለን?

የኢ.ሕአፓ ሰማዕታት ቀን በየዓመቱ ሲታወስ የሰሜን አሜሪካ እግርኳስ በሚደረግበት አካባቢ ያሉ የቀድሞና ነባር አባላት በጋራ ገንዘብ በማዋጣት የዝግጅቱን ኃላፊነት ይወስዳሉ። በፓርቲው በተፈጠረው መከፋፈል እንኳ አንደኛው ወገን የዘንድሮውን እኔ አዘጋጃለሁ ቢል ለሰማዕታት ወገኖች ሲባል እምቢታ አልነበረም። በአንድነት ታግለው በአንድ ጉድጓድ የተቀበሩ ወገኖቻችን ዓጽም አይከፈልም። ደማቸው አንድ ላይ ነው የፈሰሰው። የነሱ ደምና አጥንት ኢትዮጵያዊነትን አንፀባራቂ ነው። በዘር፣ በሃይማኖት፣ በጐሳ፣ በክልል፣ በፆታና በዕድሜ ሳይለያዩ በአንድነት ታግለው በአንድነት ተቃቅፈው የተኙ ሰማዕታትን እንዴት ሁለት ቦታ እንዘክራለን? ምነዋ ዛሬ? በቁማችን የምንከፋፈለው አንሶ ሙታንን? የሰማዕታት ቀንን? በእልህ የሚገኝ ውጤት የለምና ምናለ አንደኛችሁ ብትተዉት። ግፋ ቢል የሚከስረው የወጣ

ገንዘብ ነው። ምንም አልነበር። የሰማዕታትን ቀን ሁለት ቦታ ከፍሎ ሌላ ትዝብትና ጥቁር ነጥብ በታሪክ ላይ ጥሎ ከማለፍ የወጣው ገንዘብ ቢከስር ተመራጭ ነበር። “ለምን አደረጋችሁት?” ተብሎ ስትጠየቁ “ከፈሉት” ከማለት “ከፈልነው” ማለቱ ይመረጣል።

በየዓመቱ ካላችሁበት አካባቢ ለመጓጓዣና ለመኝታ ወጪ አውጥታችሁ፣ ከጠበበ ህይወታችሁ ለዚህ ቀን ጊዜያችሁንና ገንዘባችሁን የሰዋችሁ፣ ይህንን የወገኖቻችሁን ዝክረ ሰማህታት ለማስታወስ መጥታችሁ ሁለት ቦታ በመደረጉ አዝናችሁ ወደ ዝግጅቶቹ ከመሄድ መቅረቱን የመረጣችሁ ድክመታችን እዚህ ድረስ ነው ከማለት ሌላ ቃል አያስፈልገውም።

የኢ.ሕ.አ.ፓ መከፋፈል አባዜ አድማሱን አስፍቶ የዝክረ ሰማዕታት ቀን በሁለት ወገን ጥሪ እየቀረበ “ኢ.ሕ.አ.ፓ አንድ ሆነ” ብሎ የሀሰት መግለጫ ማውጣት፣ በየስብሰባው ማስጨብጨብ አግባብ አይደለምና እውነቱ አሁንም ኢ.ሕ.አ.ፓ በአንድነት እየሠራ አይደለም። ይህ ነው ሃቁ!

ውድ ወገኖችና የኢ.ሕ.አ.ፓ ልጆች! የኢ.ሕ.አ.ፓ መከፋፈልና በሁለት ጐራ መቀጠል አክትሞ እንደ ገና በአንድነት መጓዝ ብዙዎች የምንመኘው ነው። ቢቻል የነበሩና የተጠቆሙ የድርጅቱን ደካማ ጐኖች በሚገባ መክሮና አስተካክሎ በአንድነት መታገሉ በተገባ ነበር። ለኢ.ትዮጵያ ሀገራችን አንድነትና ለሕዝባችን ደህንነት ሲባል የነበሩ ውዝግቦችን ለቀቅ አድርጎ ወቅቱ ለሚጠይቀው የጋራ ትግል የኢ.ሕ.ኢ.ፓ በአንድነት መጓዝ ተመራጭ ነበር። ይህ ካልሆነም አርፎ ሁለት ዴሞክራሲ.ያ ዕትም እያወጡ፣ ሁለት ጋዜጣዊ መግለጫ እየሰጡ፣ አንዱ እንደቀድሞው ኢ.ሕ.አ.ፓ ሌላኛው ዴሞክራሲ.ያዊ ቅጥያውን ይዞ መጓዝ እንጂ ያልተደረገን አንድነት “ኢ.ሕ.አ.ፓ አንድ ሆነ” ብሎ ኅብረተሰቡን ግራ ማጋባት አሁንም ጉዳት እንጂ ጠቀሜታ የለውም። ተስፋ ከተቆረጠም በድክመት ላይ ድክመት መደረቡ መፍትሄ አይደለም። በአጭሩ ***<u>ኢ.ሕ.አ.ፓ አንድ የሚሆነው የችግሩ ፈጣሪዎችና ቁንጮ አመራሮችን አቅፎ እንዳልሆነ በድጋሚ ላሠምርበት እወዳለሁ።</u>***

በደምና አጥንት የተገነባው ኢ.ሕ.አ.ፓ በውስጣችን አንድ ነው!

የሰማዕታት ወገኖቻችን ደም የኢ.ትዮጵያዊነት ተምሳሌት ነው!

ቸር ይግጠመን

**አሉላ** (alulla2@yahoo.com)

**ሐምሌ** 21 **ቀን** 2007 **ዓ.ም**. (July 28, 2015)